FCC Visit DTV.gov

# ወደ ዲጂታል ቲቪ መሸጋገር

## ስለ ዲቲቪ ምን ምን ማወቅ ያስፈልግዎታል




### ወደ ዲጂታል ቲቪ (ዲቲቪ) መሸጋገር ምንድን ነው?

ባሁኑ ወቅት፡ በአየር ላይ ያሉ ብዙ ጣቢያዎች ስርጭታቸውን የሚያስተላልፉት በአናሎግ እና በዲጅታል ቲቪ መልክ ነው። ከፌብሪዋሪ 17, 2009 በኋላ፡ ባለ ሙሉ ሃይል ቲቪ ጣቢያዎች ስራጭታቸውን የሚቀጥሉት በዲጅታል ብቻ ይሆናል። ወደ ዲቲቪ መሸጋገር በአየር ላይ በነፃ ቴሌቪዥን በሚያዩ ሰዎች ላይ (ጣራ ላይ የተሰቀለ ወይም "የጥንቸል ጆሮ" በሚመስል አንቴና የሚሠራ) ለውጥ ያስከትላል። እርስዎ  በአየር ላይ የሚተላለፉትን ፕሮግራሞች የሚያዩት በአናሎግ ቲቪ ከሆነ፡ ከፌብሪዋሪ 17, 2009 በፊት እርምጃ መውሰድ ይኖርብዎታል።

### የማሰራጫ ጣቢያዎች ወደ ዲጂታል የሚለውጡበት ምክንያት ምንድን ነው?

የአየር የግንኙነት መስመር ለፓሊስ፡ ለእሳት አደጋ፡ ለአስቸኳይ እና ፈጥኖ ደራሽ ግንኙነት ነፃ ለመልቀቅ የፌዴራል ሕግ ለውጡ እንዲደረግ ስላዘዘ፡ በተጨማሪም አሰራጪዎች የተሻለ ጥራት ያለው ምስል፡ ድምጽ እና የተለያዩ አማራጭ ፕሮግራሞች እንዲያስተላልፉ እና ሽቦ አልባ የሆኑ የንግድ አገልግሎቶች በስፋት ለደምበኞች እንዲያቀርቡ ለማድረግ ነው።

### ለመዘጋጀት ምንድን ማድረግ አለብኝ?

ሶስት አማራጮች አለዎ:

**1** **የአናሎግ ቲቪዎን ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን ጋር ያገናኙ።** ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥኖች በየሱቁ አሉ ዋጋቸውም አንድ ጊዜ የሚከፈል $40-$70 ነው።  ለእነዚህ ሳጥኖች መግዣ ለመርዳት የዩ. ኤስ. መንግሥት ሁለት የ$40 ኩፓን ለአንድ ቤተሰብ በእርዳታ ያቀርባል። ስለኩፓኖቹ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.dtv2009.gov ይጎብኙ፡ ወይም ይደውሉ በ1-888-388-2009 (ድምጽ) ወይም 1-877-530-2634 (ቲቲዋይ) ይደውሉ። እንዲሁም፡ አሁን ባለዎት የስርጭት መቀበያ አንቴና የአናሎግ መስመሮችን 2-51 ስርጭትን በጥሩ ሁኔታ የሚቀበሉ ከሆነ፡ አዲስ አንቴና አያስፈልግዎትም። **ወይም**

**2** **የዲጅታል ቴሌቪዥን ይግዙ (በውስጡ ዲጂታል ማዞሪያ ያለው ቲቪ)።** ዲጅታል የቴሌቪዝን ስርጭት ለማየት፡ ሃይ ዴፍኒሽን ቲቪ (ኤችዲቲቪ) አ<u>ስፈልግዎትም</u>። የሚያስፈለግዎት <u>ዲጅታል</u> ቲቪ ብቻ ነው (ወይም ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን ጋር የተያያዘ አናሎግ ቲቪ)። እንዲሁም፡ አሁን ባለዎት የስርጭት መቀበያ አንቴና የአናሎግ መስመሮችን 2-51 ስርጭትን በጥሩ ሁኔታ የሚቀበሉ ከሆነ፡ አዲስ አንቴና አያስፈልግዎትም። **ወይም**

**3** **በክፍያ የሚቀርብ የቲቪ አገልግሎት ያግኙ፡** የአካባቢ ስርጭቶችን እንደ ኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ ካለ አቅራቢ በክፍያ አገልግሎቶችን የሚያገኙ ከሆነ፡ ቴሌቪዥንዎ ለዲቲቪ ስርጭት ተዘጋጅቷል። የክብል ኩባንያዎች ማናቸውንም የስርጭት መስመራቸውን ወደ ዲጅታል የማሸጋገር ወይም የመቀየር ግዴታ <u>የለባቸውም</u>።   ሆኖም እርስዎ አናሎግ ቲቪ ካለዎት በሚከፍሉት አገልግሎት ሰጭ በኩል የአካባቢ ስርጭቶችን <u>የማይቀበል</u> ከሆነ፡ በዚያ ቲቪ የዲጅታል የቴሌቪዝን ስርጭት ለማየት፡ ከዲጅታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን ያስፈልግዎታል።

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት:**

1-888-CALL-FCC | DTV.gov | 1-888-TELL-FCC (TTY)

# THE DIGITAL TV TRANSITION

United States Environmental Protection Agency

## What You Can Do with Your Analog TV

## የአናሎግ ቲቪዬን የአገልግሎት ዘመን እንዴት ማርዘም እችላለሁ?

አናሎግ ቲቪ ካለዎትና ነጻ የምድር ለምድር ሥርጭቶችን የሚቀበሉ ከሆነ፤ ቲቪዎን ከዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሣጥን ጋር በማገናኘት ወይም በክፍያ አገልግሎት ከሚሠጥ የቲቪ አገልግሎት ሰጭ ጋር ደንበኝትን በመመስረት የቲቪዎን የአገልግሎት ዘመን እንዲያራዝሙ የየዩኤስ አካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ ያበረታታዎታል።

ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሣጥን ሲገዙ፤ የENERGY STAR መለያ ያለበትን ይግዙ። በENERGY STAR-ብቁ የተደረጉ ቀያሪ ሣጥኖች ከተራ ቀያሪ ሣጥኖች ያነሰ የኃይል ፍጆታ አላቸው። በዩ.ኤስ. ውስጥ የሚሸጡ ሁሉም ቀያሪ ሣጥኖች የENERGY STARን ቴክኒካዊ መስፈርቶች ካሟሉ፤ በየዓመቱ የ823 ሚሊየን ኪሎዋት-አወርስ ሃይል እንቆጥባለን።

በENERGY STAR ብቁ የተደረጉ ሞዴሎችን ዝርዝር ከwww.energystar.gov/products ኘት ይችላሉ። (ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሣጥኖችን ይምረጡ)።

## የቀድሞውን ቲቪዬን ካልፈለግኩት ምን ላድርገው?

**ሪሳይክል ያድርጉት!** አዲስ ዲጂታል ቲቪ ለመግዛት ከወሰኑና የቀድሞውን ቲቪዎን ከዚህ በኋላ የማይፈልጉት ከሆነ ሪሳይክል የማድረጊያ ዕድሎችን ያፈላልጉ። ቲቪዎችን ሪሳይክል የማድረጉ ተግባር ከሰርኪዩት ቦርዶች፣ ከሜታል ሽቦዎች፣ ከባለ ሊድ መስታወቶች እና ፕላሲቲኮች ዋጋ ያላቸውን ማቴሪያሎች ለማግኘት ያስችላል። በአካባቢዊ ለሚገኘው የአደገኛ ውጋጅ ማሰባሰቢያና ሪሳይክል ማድረጊያ ፕሮግራም በመደወል በቀጣይ የሚደረጉ የቲቪና የሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ሪሳይክል ማድረጊያ ተግባርን ስፖንሰር ያደርጉ እንደሆን ይጠይቁ። በተጨማሪም በአቅራቢያዎ ስለሚገኝ የሪሳይክሊንግ ፕሮግራም ለማወቅ የሚከተሉትን ድረ ገጾች ይጎብኙ፡-

ለዜሌክትሮኒክስ ሪሳይክሊንግ ግብዓታዊ ኃብቶችንና ቦታዎችን የመለየቱ ተግባር የኢአርኤ የአገልግሎት አጽድቆት አካል አይደለም።

EARTH 911 www.earth911.com/electronics የኧርዝ 911 ዚፕ-ኮድ ላይ የተመረኮዘ የፍለጋ ኤንጂን በማኅበረሰብዎ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ምርቶችን ሪሳይክል የማድረጊያና መልሶ የመጠቀሚያ አማራጮች እንዲያገኙ ያስችልዎታል።

National Recycling Coalition www.nrc-recycle.org/localresources.aspx ይህ ገጽ የግዛት የሪሳይክሊንግ አገልግሎት ሰጪዎችን የድረ ገጽ ሊንኮች ይሰጥዎታል። በርካታ ማኅበረሰቦች ልዩ የመሰብሰቢያ ሪሳይክል የማድረጊያ ቀናት ያሏቸው ሲሆን በየድረ ገጾቻቸው ላይ ተመልክተዋል።

My Green Electronics www.mygreenelectronics.org ከዚህ የተጠቃሚዎች የኤሌክትሮኒክስ ማኅበር ገጽ ላይ ‹‹አረንጓዴ›› የኤሌክትሮኒክስ ምርቶችን ስለመግዛት ይበልጥ መረጃዎችን ማግትና ሪሳይክል የማድረግ ዕድሎችን ማፈላለግ ይችላሉ።

ለአብዛኞቹ የሚሠሩ የኤሌክትሪኒክስ ምርቶች ልገሳ መልካም አማራጭ ነው። ለዚህም ምክንያቱ መልሶ መጠቀምን የሚያቀላጥፍና የምርቱን የአገልግሎት ዘመን የሚያረዝም መሆኑ ነው። ሆኖም ወደ ዲጂታል ስርጭት ከመሸጋገር ጋር ተያይዞ በርካታ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አናሎግ ቴሌቪዥኖችን ላይቀበሉ ይችላሉ። እባክዎ ቴሌቪዥንዎን ከማስወገድዎ በፊት ከድርጅቶቹ ጋር ይገናኙ።